በስደት የኢትዮጵያ መምህራን ማህበር አባላት አስተባባሪ ኮሚቴ
Coordinating Committee of Exiled Members of Ethiopian Teachers' Association

የተሰጠ መግለጫ

ታሕሣሥ 16 ቀን 2008 ዓ.ም

የጋራ ጠላታችንን በጋራ እንታገል!!

ኢትዮጵያውያን ባብዛኛው ስፍራ፣ ባብዛኛው ቁጥራችን ለአገራዊ ጉዳዮቻችን ትኩረት ሰጥቶ አፋጣኝ መፍትሔ መሻቱ ላይ የወያኔ አፍዝ አደንግዝ ነግሶብን ቆይቷል። ስለአገራችን ሉዓላዊነት ፣ ስለሕልውናችን፣ ስለወደፊት ዕጣ ፋንታችን ወዘተርፈ ከግለሰቦችም ከቡድኖችም ቢነገረንም ዕዝነሕሊናችን ያደመጠ አልመሰለም።ከዚህ አንፃር አገር እንደአገር ፣ ሕዝብም እንደሕዝብ፣ እንዳይቀጥል የሚጎነጎነው ሴራ ቀጥሏል። ከመሐላችን የበቀሉ አሜኬላዎች እኛን መስለው ተደራጅተው ፣ በቡድን ተቧድነው ግን ከአገርና ከሕዝብ በተቃራኒ ቆመው ሊያጠፉን፣ ሊይስጠፉን ወደ ጠርዝ እየገፉን ይገኛሉ።

እውነት ለመናገር ተግተው የሠሩበት የዘር ፖለቲካቸው ዘላቂ መሆኑ ባይታይም እስከተወሰነ ደረጃ ለጊዜያዊም ቢሆን ሰምሮላቸዋል፣ ማደናገሪያቸውና የውሸት ፕሮፖጋንዳቸውም እንዲሁ።ለዚህ ነው በሶማሌ፣ በአፋር፣ በጋምቤላ ፣ በሲዳማ፣ በወላይታ፣በሀድያ፣ ----ሰዎች ሲጠቁና ለእዴጋ ሲጋለጡ ከአካባቢው ሕዝብ ባለፈ የሁሉም የኢትዮጵይውያን ችግር፣ ጥቃትና በደል ተደርጎ የማይነሳ እየሆነ የቆየው።ሙስሊም ወገኖቻችን የዕምነትና በነፃ የመደራጀት መብቶቻቸው እንዲከበር እየጠየቁ በሰላማዊ አካሄድ ከሶስት ዓመታት በላይ ሲታገሉ ከሌላው ማህበረሰብ የሚጠበቀው እገዛ በቂ አልነበረም። መምህራን በኢሕ ከተማና በጎንደር አድማ በመቱበት ጊዜ ተቃውሞው በነዚያ አካባቢዎች ተወስኖ በመቅረቱ ብዙ ጉዳት በመምህራን ላይ ደርሷል። አሁን በቅርቡ የአዲስ አበባ ከተማን የማስፋፋት የወያኔ ፕላን ጋር በተያየዘ በኦሮሚያ ክልል የሚገኙ የዩኒቨርስቲ ፣ ከፍተኛና አንደኛ ደረጃ ተማሪዎች የተቃጣጠለውና የሕዝብም ድጋፍ የነበረው ተቃውሞ በሌሎች ክልሎች መደገፍና መተባበር ሲገባው ይህ አልሆነም። ሕዝቡ ላነሰው የመብት ጥያቄና ሰላማዊ እንቅስቃሴ አግባብ ያለው መልስ መስጠት ይገባው የነበረው በመንግሥት ስም የተቀመጠው የወያኔ ሥርዓት ለሕዝብ ጥያቄ ቀና መልስ እንዲሰጥ ተፈጥሮያዊ ባሕርዩ ስለማይፈቅድ ኦጋዚ ጦር በሕዝብ ውስጥ አዝምቶ ጦሩ በወሰደው እርምጃ የሰው ሕይወት አልፏል፣ እስራት፣ድብደባ፣ መሰወር፣ ማሳቃየት፣ የንበረትና የሀብት ውድመት ደርሷል። በስደት የኢትዮጵያ መምህራን ማህበር አባላት አስተባባሪ ኮሚቴ ይህን ድርጊት በጥብቅ ያወግዛል፤ ይቃወማል። በእብሪት ዜጎቻችን የገደሉ የኦጋዚ ጦር አባላት በአስቸኳይ ለፍርድ እንዲቀርቡ ይጠይቃል።

ሕዝብ ብሶቱ በዝቶ አደባባይ ወጥቶ ተቃውሞ ሲያሰማ የማይሆንና የማይመስል ስም እያወጡ የወያኔ ባለሥልጣናት ሊኮንኑ ይቃጣሉ። ያለበታው፣ ያለጊዜው፣ ያለበቂ ምክንያት ካወጡት የሽብርተኝነት ሕግ ዘለላ ሐረግ እየመዘዙ ንውሐንን ወንጅለው ወደ እስር ለማዳፋት ይጠቃመበታል። ከርሃብ፣ ከእርዛት፣ከበሽታና ከስደት --------ያላዳነ ባዶ የሁለት አኃዝ የኢኮኖሚ ዕድገት እየጠቀሱ ልማታችንን ለማደናቀፍ የሚል የማጭበርበሪያ ጩኸት ያሰማሉ።መቼም አያስችለው የለ ሆኖ ይህን ሁሉ የግፍ ቀንበር ተሸክመን እንድንኖር ተገደናል፤ መኖር ከተባለ።

የግፍና የጥቃት ጥርቅም የሰው ልጆች ከሚችሉት ገደብ በላይ ሲደርስ ሕዝባዊ አመፅ የታሪክ ግዴታ ሆኖ ይከሰታል።ቀደም ሲል በተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎች ቦግ አልም እያሉ ከታዩት ተቃውሞች ያሁኑ በኦሮሚያ ክልል የተከሰተው ሕዝባዊ ተቃውሞ እስካሁን ከታዩት ሰፊ አካባቢዎችን በመሸፈኑና እምቢተኝነቱ ጠንከር ማለቱ ወያኔን አርበትብቷል።ተቃውሞና እንቅስቃሴው ት/ቤቶችን ማዕከል በማድረጉ ሕዝባዊ ይዘት እንዲላበስ አድርጓል። ትምህርት ቤቶች ከሁሉም የኑሮ ረድፍ የሚመጡ ተማሪዎችና መምህራን መናኸሪያ ናቸው። ስለሆነም የህዝቡ ትግል ከኢትዮጵያ ሉዓላዊነትና ከሕዝብ አንድነት በተቃርኖ ከቆሙ ኃይሎች እንዳይጠለፉ ወቅታዊና ታሪካዊ ኃላፊነት አለባቸው።

መምህራንና ተማሪዎች ለአገርና ለሕዝብ ሉዓላዊነት ፣ ለሰብአዊ መብቶች መከበር፣ ለመልካም አስተዳደርና ፍትሕ ስምረት ባጠቃላይ ለዲሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታ ዘራቸው፣ አካባቢያቸው፣ ቋንቋቸው፣ ባህልና ዕምነታቸው በልዩነት አምድ ላይ የሚያቆማቸው አይሆንም።የትም ይሁን የት ሕዝባዊ ጥያቄዎች ሲነሱ በጋራ እንዳይስተጋቡ የወያኔ ከፋፋይ ፖሊሲ ጋሬጣ እንዲሆን መፈቀድ የለበትም። የዘር ፖለቲካው ነፃብራቅ በየቦታው በሚነሱ ግጭቶች ታይቷል።ይህን የልዩነት አደገኛ ግድግዳ መስበር ያስፈልጋል። የመሬት ነጠቃውና ቅርምቱ ደርቷል። የመሬት ለአራሹ ጥያቄ ያልተመለሰ መፈከር ሆኖ ቆይቷል። ይህ ሁሉ በሕዝብ ላይ የሚፈጸመው ግፍ ምላሽ የሚያገኘው የሥርዓት ለውጥ ሲመጣ ነው። ለዚህ ደግሞ የልዩነት ግድግዳዎችን በመስበር የጋራ ጠላታችን በሆነው የወያኔ አገዛዝ ላይ በጋራ መቆምና መታገልን ይጠይቃል።ከዚህ በመነሳት በስደት የኢትዮጵያ መምህራን ማህበር አባላት አስተባባሪ ኮሚቴ አገር ለማዳንና የሥርዓት ለውጥ ለማምጣት ኢትዮጵያውያን ሁሉ በጋራ እንዲነሱ ጥሪ ያቀርባል።

ሕዝባዊ አመጹ ይፋፋም!!
ቅድሚያ አገርን ለማዳን!!
የወያኔን የመከፋፈል ፕሮፖጋንዳ እናከሽፍ!!
መሬት ለአራሹ ይሁን!!

P.O.Box 16632 Saint Paul, MN 55116 • Tel.: 403-402-0334 • Email: eta1941@yahoo.com